# ታዛቢው ብሎታል

በስራው አስተዋይ ፣ ሁሌ ረጋ ብሎ
ሲናገር ሲራመድ ፣ በደንብ አስተውሎ
የማይቆረጠም ፣ ብርቱ የብረት ቆሎ
የጎንደር የጎጃም ፣ የሸዋ የወሎ
በቀል ሳይወጣ ፣ ገዳዮቹን ገሎ
ባስር እጥፍ ድርብ ፣ ካልሆነ አስከፍሎ
እንቅልፍም የለውም ፣ እንዴት ተደላድሎ ።

ታግሶ አሳልፏል ፣ አሁንስ ይበቃል
አልማር ያለንም ፣ ማስተማሩን ያውቃል
በትሩን ያውቁታል ፣ ከንግዲህ ያጠቃል
በሳር በቅጠሉ ፣ አንበሳው ተንቋል
እከክና እከካም ፣ ከምድር ይፋቃል
አማራም በተራው ፣ ሲያለቅሱ ይስቃል ።

ወንድሜ ነው ብሎ ፣ ታግሶ በቻለው
ለፍቅር መገዛት ፣ ፍርሃት መሰለው
ደንቆሮ ሆነና ፣ እንዲያው ባያድለው
ወርቁን እንዳሸዋ ፣ ሊያራክስ ከጀለው
ታግሶ ቢንቀው ፣ ደካማ ነው አለው ።

ጥጋብ የማይችለው ፣ የዕውቀት መፃጉ
መቼ ያውቀውና ፣ ድንቁርና ደጉ
ይጀነን ጀመረ ፣ እንዲያው ያለ ወጉ
በማን እንደመጣ ፣ ነፃነት ማዕረጉ
የጣልያን አሽከሮች ፣ ትላንትን ዘነጉ
አንበሳን ይጋፋል ፣ አህያውም በጉ ።

ጨክኖ ሲነሳ ፣ አማራው ወገኔ
ሽሽት ወደ አውሮፓ ፣ ወጥኗል ወያኔ
ለትግሬው ጥገኛ ፣ ይብላኝለት ያኔ
ለፈፀመው በደል ፣ ለሰራው ኩነኔ
ላማራው ሲሰግድ ፣ ያሳየኛል አይኔ ።

ይህን አስተውሉ ፣ ትንቢቴ ነውና
ዛሬ ተረት ሆኖ ፣ ነገን ይተካና
ሁሉም ዕውን ሲሆን ፣ ዛሬ ስትሆን አምና
ታዛቢው ብሎታል ፣ ማለት አይቀር ገና ።

ታዛቢው

May 23, 2018